09/07/98

Radio Rainbow
ቀስተ ደመና ሬዲዮ
Radio Arc - En - Ciel
C/o P.O Box 140 104. 53056 BONN. GERMANY - Fax: (49) 228 / 61 23 81

ቀስተደመና 09/07/98

## ኢህአዴግ ዉስጥ የሻብያ ጉዳይ አስፈፃሚዎችን እንዴት እንለያቸዉ?

ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሻብያ ደግሞ አስመራን እንደተቆጣጠሩ ቅጥረኞቹ በሃገራችን ለመትከል ባሰቡት የጥላቻና የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ ተማምኖ ኢሳያስ አፈወርቂ ለኢትዮጵያዉያን "የመቶ አመት የቤት ስራ ሰጥቻቸዋለሁ" እያለ ዉስጥ ውስጡን ይደነፋ እንደነበረ የማያዉቅ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለንም:: ባለፉት ሰባት አመታት የኢህአዴግ/ህወሃት መሪዎች ሃገራችንን ለእንደዚህ አይነቱ ሴራ ሲያመቻቹና በያለበት ግዜ ጠብቀዉ ሊፈነዱ የሚችሉ የጥላቻና የመከፋፈል ፀምቦች ሲቀብሩ ቆይተዋል:: ዛሬ በተከሰተው ውጥረትና ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ ላይ ባለው ጦርነት ሳቢያ ኢሳያስ አፈወርቂ ይህንን የአጥፍቶ መጥፋት ፖለቲካዉን በይፋና በአደባባይ ይዞ ወጥቷል:: ዓላማዉ ኢትዮጵያን ለማተራመስ እንደሆነና ለዚህ ደግሞ ብቃት እንዳለዉ እየለፈፈ ይገኛል::

የሻብያ መሪዎች ይህንን የመሰለ ዛቻ ሴላዉ ቀርቶ በዓለም መገናኛ ብዙሃን ሳይቀር ለመለንዘር የበቁት በኤርትራ ሃብት፣ የሰዉ ሃይልና የመሣሪያ ብዛትና ጥራት ተማምነዉ አይደለም:: የሚተማመኑት የኢህአዴግ የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ በቀበራቸዉ የጥላቻ ፀምቦች ÷ ፀረ ዲሞክራሴያዊ አገዛዙ በሃገራችን ሰላም ላይ በደነቀራቸዉ መሰናክሎች፤ የብሄራዊ እርቅና የብሄራዊ ውይይትን አሻፈረኝ በማለት በሚነዛው ውዥንብርና በነዚህ ሁሉ ፀረ ህዝብ ፖሊሲዎች መቀጠል እንደሆነ ግልፅ ይመስለናል::

የኢህአዴግ አደገኛ ፖለቲካ በሀገራችን ሰላምና የእድገት ሂደት ላይ ሊያስከትላቸው የሚችላቸውን ጠንቆች ጠንቅቀዉ በመገንዘብ ሃቀኛ ኢትዮጵያውያን በሙሉ የጥላቻን ፖለቲካ ተቃውመው ለብሄራዊ እርቅና ለኢትዮጵያ ህዝቦች እኩልነትና ወንድማማችነት: የግፍ አገዛዝን ተቃውመው ለዲሞክራና ለሰብአዊ መብቶች: ለጠላቶቻችን ብቻ የሚያመችን አደገኛ ዉዥንብር ተቃውመው ለጋራ አማራጭ የጋራ ትግል የሚሉ መፈክሮች አንግበው ትግሉን መልክ ለማስያዝና ህዝባዊ የሆነ ዓላማ ለማስያዝ ብዙ ጥረት አድርገዋል :: ከዚህ አንጻር ሲታይ የቀድሞዉ የፓሪስ ጉባኤ አስተባባሪ ኮሚቴ አባል ድርጅቶች ባለፈዉ ሳምንት በአምስተርዳም ከተማ ተሰብስበው ለዲሞክራሲያዊ ሂደት: ለነፃ ምርጫና ለዲሞክራሲያዊ ህገ መንግስት የጋራ አማራጭ አቅርበው በጋራ ለመታገል መወሰናቸውን የኢሳያስ አፈወርቂን የትርምስ ዛቻ ለማክሸፍ አንድ ታሪካዊ ምእራፍ ወደፊት ተራምደዋል ማለት ይቻላል::

ይህን የተቃዋሚዎች የጋራ ሂደት በኢህአዴግ/ወያኔ ውስጥ ያሉ የኢትዮጵያን ጥቅም እናስከብራለን ብለዉ የተነሱ ኃይሎች እንደሚደግፉት እንደማንጠራጠር ሁሉ አሁንም በዚህ ድርጅት ወስጥ ያሉትና በሙሉ ገና ያልተሸነፉት የሻቢያ ጉዳይ ፈፃሚዎች እንደሚቃወሙት መጠራጠር አይቻልም::

የሻቢያ አብሪተኛ አቋምና ትምህርት ገበታ ላይ ባሉ ህፃናት ላይ ሳይቀር የፈፀመዉ ግፍ በኢህአዲግ ዉስጥ ባሉት ጉዳይ አስፈፃሚዎች ችግር እንደ ፈጠረባቸዉና እንደ ቀድሞዉ ሽንጣቸዉን ገትረዉ ሊሟገቱለት የሚችሉበት ሁኔታ ላይ እንዳይደሉ ግልፅ ነዉ:: በመሆኑም

እነዚህ ሰርጎ ገቦች የትግልና የተልእኮ ስልት በመቀየር ዛሬ ላይ ላዩን ሲታዩ የሻቢያ ዋና ተቃዋሚዎች መስለዉ ለመቅረብ ሲገደዱ እያየናቸዉ ነዉ:: ሁሉም ፀረ ሻቢያና አገር ወዳድና የኢትዮጵያን ክብርና ጥቅን አስከባሪ መስሎ ላይ ታች በሚልበት ሁኔታ ታዲያ ጉዳይ አስፈፃሚ ዎቹን በምን እንለያቸዉ?

በልፊፋ ደረጃ ዛሬ ሁሉም አንድ ዓይነት ጩሀት በሚያሰማበት ወቅት ስለሆነ በኢህአዴግ አመራር ዉስጥ እነአገሌ አገር ወዳድና ዲሞክራቶች ናቸው÷ እነእገሌና አገሌ ደግሞ አዉቀዉም ሳያዉቁም የነሻቢያን መሪዎች እርኩስ አላማ የሚያራምዱ ከሀዲ ሰርጎገቦች ናቸው ማለቱ አሰቸጋሪም ትርፍም ይመስለናል:: እርግጠኛዉ መለኪያና ማጋለጫ የፖለቲካ አቋማቸዉ ብቻ ነዉ:: ሰባት አመት ሙሉ የተከተሉት የጥላቻና የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲያቸው መቀጠሉ ለሻቢያ መሪዎች አገር የማተራመስ አጀንዳ ሁኔታዎችን እያመቻቸላቸዉ በግልፅ እያየን "ምንም የፖለቲካ ለዉጥ አያስፈልግም" ይሉናል:: ዜጎች በጠራራ ፀሃይ በአደባባይ በጥይት እየተደበደቡና የሰላሙ የትግል መስክ እየጠበበ ኢትዮጵያዉያን በየእለቱ በሚጨምር ቁጥር ወደ ትጥቅ ትግል ለማምራት እየተገደዱ አገር ሰላም ነዉ ይሉናል:: በአለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር ሃገራችን በሰብአዊ መብት ረገጣ ነጋ ጠባ ስትኮነን፤ በፖለቲካ እስረኞ ብዛት የዉርደት ሪከርድ ስትከናነብ "ከደረቅ ወንጀለኛ በቀር ምንም እስረኛ የለንም" ይሉናል:: ሃገራችን የብሄራዊ እርቅና ትርጉም ያለዉ ብሔራዊ ዉይይት ያስፈልጋታል ሲባል ይህ ፖለቲካ የኢሳያስን ሤራ ለማክሸፍና ሃገራችንን ከጥፋት ለማዳን ምን ያህል አጣዳፊ እንደሆነ ጠንቅቀዉ ስለሚያዉቁት ይህንን የኢትዮጵያዉያንን መቀራረብ ሂደት በሰበብ አስባቡ ይቃወማሉ::

እነዚህ ጉዳይ ፈፃሚዎች በዚህ መልክ ፀረ ህዝብ ተልእኳቸዉን አስካካሔዱ ድረስ ማንም ኢትዮጵያዊ በፀረ ሻብያ ድንፋታዎች መወናበድ የለበትም:: የኢትዮጵያ ህዝብ በረዥም ዘመናት ትግሉ ተራ ልፈፋን ከተጨባጭ ድርጊት መለየት ይችላልና ዛሬ በሃገራችን ዲሞክራሲን ለማጎልበት ለነፃና ርእታዊ ምርጫ በተጨባጭ የማይቆሙትን÷ ለሰዉ ልጅ መብቶች መከበር በሀቅ የማይታገሉትን÷ ለብሔራዊ እርቅና ትርጉም ላለዉ ~~ብሔራዊ [illegible]ትንና~~ ለዚህም አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር ድርጅታቸዉ በየእስር ቤቱ ያጎራቸዉን የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈታ ከህዝብ ጎን የማይቆሙትን መሪዎች ሁሉ አሁንም የሻብያ ጉዳይ ፈፃሚዎች አድርጎ በመቁጠር ይታገላል።።

ቀስተ ደመና ሬዲዮ የሰላምና የወንድማማችነት ድምፅ ሬዲዮ